"ማን ያውራ የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ"

ኢህ አፓና ህወሓት ጥላቻቸው እስከ መጠፋፋት ሊያመር ያስቻለው ምክንያት ምን ነበር?

ከበየነ ገብራይ፣ ደንማርክ ክፍል 1

መግቢያ

የኢህ አሰ ታሪክ ከበትና 1972 እስከ 1985 በተከታታይ እንድተርክ ያነሳሳኝ አሁን ስለተማረኩት የኢህ አፓ አመራሮች ግድያን በተመለከተ በጻፍኩት ላይ እንደ ወንድሜ ገረብ ወዲ ፃናና ወንድሜ አለማ ዶላ ዓይነቶቹ እያደረጉት ያለው ምልልስ ዓይነት ክርክሮች በየዜው በተለያዩ ወጣት ምሁራን በተገኘው አጋጣሚ ስለ ያትውልድ (ያትውልድ ስል በኢህ አፓ፣ በመኢሶን፣ በኢዴህ፣ በደርግ፣ በህወሓት፣ በግገሓት፣ ተሰልፈው የታገሉትን ሁሉ መሆኑ እንዲታውቅልኝ) ሲነጋገሩ ሁለት ጫፍ ይዘው የሚያደርጉት ክርክርና አሁን ስልጣን ላይ ያሉት የህወሓትና የያኔው ኢህ ዴን የዛሬው ብ አዴን መሪዎች በተለይ ኢህ አፓና ሰራዊቱ በተመለከተ ኢህ አፓ በ 1972 በሰራዊቱ ወስጥ የተከሰተው ብተና ላይ እንዳለ ድርጅቱ ተበታትኖ የኢህ አፓ ትግል ያኔ እንዳከተመለት አድርገው ወጣቱ ትውልድን ለመሳመን የሚያደርጉት ሩጫ ትክክል አልመሆኑን ቢያንስ በዚህ ሶሽያል ሚዲያ የሚጠቀመው ወጣቱ ትውልድን ማሳወቅ አለብኝ በሚል ነው። ይህን ኣሁን በ 22 ኛ ክፍል ላይ ደርሶ ያለውን የኢህ አሰ ትጥቅ ትግል ትረካ ለወደፊት የምቀጥልበት ሆኖ፣ በተወሰነ ደረጃ የኢህ አፓና የህወሓት የርስበርስ ጥላቻ መሰርቱ ምንድን ነው ለሜልው ጥያቄ ወጣት ምሁራን ተማራማሪዎች በጥልቀት እንድትመረምሩት ይረዳ እንደሆነ በሚል በመጨረሻዎቹ የደርግ ውድቀት አከባቢ ሁለቱ ሃይሎች የደርግ ውድቀት እየተቃረበ መሆኑ ተረድተው ሲያደርጉት የነበረውን ዝግጅት እኔ ይበልጥ የማውቀው የነበረ በኢህ አፓ በኩል ሲደረግ በነበረ ዝግጅት ላይ ምስክርነቴን ለፈስቡክ አንባቢያን በሚያመች መንገድ አጭር ባጭር እየከፋፈልኩ በተከታታይ ለማቅረብ ፈለግኩና ክፍል 1 የኸውላችሁ። ኢህ አፓና ህወሓት ከምስረታው ጀመረው ያልተስማሙ፣ በትግራይ፣ በወልቃይት፣ በቋራ በጥይት የተፋለሙና የተገዳደሉ ድርጅቶች ለመሆናቸው ሁሉም የሚያውቀ ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ነው። በሁለቱ ድርጅቶች መካከል በተደርጉት ጦርነቶች በርካታ ወጣቶች ከሁለቱም ወገን ተሰውተዋል፣ አካላቸው ጎድሏል። ይህ ጦርነት ማን ጀመረው፣ ማን ነበር ጦርነቱ ባንዱ መጥፋት እንዲያከትም ይሰራ የነበረው የሚለው ጥያቄ ለወደፊት የሁለቱም ሃይሎች የትግል ጉዞ በትክክል ገምግሞ የሚያቀርብ ገለልተኛ አካል እስከሚገኝ በሁለቱም በኩል የነበርን አባላት የምናውቀውን ከማሳውቅ የዘለለ ሌላ ነገር ማድረግ አንችልም። እንደኔ ፍላጎትና እምነት በአጋጣሚ በህይወት የተረፍን የኔው ትውልድ አባላት ዛሬ ላይ ቆመን፣ ትናትናን ስናስታውስ ትናንትና በመካከላችን የተፈጸመው ስህተት፣ ትናትና የፈጸምነው ድክመትና ችግር ለዛሬውና ለነገው ህይውታችን ልንሰራው ለምንፈልገው ስራ ፈጽሞ እንቅፋት ሊሆነን አይገባም። ባጋጣሚ በህይውት የተረፍን የኢህ አፓ፣ የመኢሶን፣የህወሓት. . . ወዘተ አባላት ዛሬ ላይ ቆመን ትናንትናና ፍጻሜዎቻቸውን ስንዘክር ልናፍረበት፣ ልናዝነበት ይገባናል እንጂ ልንኩራራበትና ለናቅራራበት ፈጽሞ አይገባም። ትናትና ከሁሉም ወገን የወድቁ ወንድሞቻችና እህቶቻችን መስዋዕትነት እኩል ልያስዝነን እንጂ ኣሁን አንዳነዶች እንደሚያደርጉት ያንዱ ወገን መስዋዕትነት ቅዱስ፣ የሌላው ወገን ደግሞ እርኩስ አድርጎ ማቅረብ እጅግ ትልቅ ስህተትና ውንጀልም ጭምር ነው። ወደድንም ጠላንም ለተፈጸመው ልማት ሆነ ጥፋት፣ ሁላችን የየድርሻን በየደረጃው አበርክተናልና፣ ታሪኩም ጥሩዉም ቆሻሻውም ሁሉ የጋራ ታሪካችን ነውና። የትናንቱ ወጣት ትውልድ፣ የዛሬው ሽማግሊዎች የሆን ባጋጣሚ በህይወት የተረፍን፣ ለዛሬ ወጣቱ ትውልድ የትናንቱ ታሪክ ስናስተላልፍ እንደ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን በታሪክነቱ ሚዛኑን ጠብቆ ኡነቱ እንዲተላለፍ ትልቅ አደራና ግዴታ በላያችን ላይ ወድቋል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ዛሬ እንደ ትናንቱ በድርጅት ሳይሆን በግለሰብ

ኢትዮጵያዊነት የምናምን፣ መጻኢቷ በእኩለነት ላይ የተመሰረተች አንዲት ዴሞክራሲያዊትና ሉዓላዊት ኢትዮጵያ የምንመኝ የትናንቱ ወጣቶች የዛሬ ሽማግሌዎች የምናውቀውን ኡነታ እንደወረድ ለውጣቱ ማሳወቅና ፍርዱን ለዛሬ ወጣት ትውልድ መተው መቻል አለብን። የዛሬው ወጣት ትውልድ ደግሞ ከአንዱ ወገን የሚሰማውን ብቻ ይዞ ከመጋለብና ሌላውን ወገን ሳይሰማ መኮነን መቆጠብ አለበት። የዛሬ ወጣት ትውልድ ኢህ አፓ፣ መኢሶን፣ ኢዴህ፣ ደርግ ኢሰፓም ሳይቀር በሀገራቸው ገብተው ፍርዳቸውን በኢትዮጵያ ህዝቦች እንዲያገኙ የምችሉበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት እንጂ አሁን ስልጣን ላይ ከ 25 ዓመት በላይ ተቀምጦ ሁሉንም ዘግቶ ሀገሪቷን እና ህዝቦቿን ወደማየውጡበት ገደል እየገፋ ያለው ኢህ አዴግ በነዚህ ሀይሎች ላይ እየዘረጋው ያለው የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ፈጽሞ መሆን የለበትም። ከኢህ አዴግ ፕሮፓጋንዳ ውጭ በያትውልድ አባላት የሚጻፉትንና የሚነገሩትንም በሚገባ ማንበብና ማዳመጥም መቻል አለበት። ለምሳሌ ስለ ኢህፓ ሁሉም የመሰለውን ለመናገር መብቱ የተጠበ ሆኖ፣ ኢህ አፓ ፈጸማቸው ለሚባሉ ወንጀሎች ሆነ ድክመቶች ራሱ የኢህ አፓ ገዳይ የሆነው ህወሓት ዳኛም መስካሪም ሆና የሚሰጠው ፍርድ ሆነ ምስክርነት መቆም አለበት። ይህ እንዲቆም ደግሞ ወጣቱ ኢህ አዴግ የዘጋውን በርከ እንዲከፍት፣ ባለው ህግ መሰረት እሱም እኩል እንዲዳኝ መታገል አለበት እንጂ፣ ራሱ የዚህ የቅጥፈትና የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ፈጽሞ መሆን የለበትም። በነገራችን ላይ ይህ ስል በግሌ ከጥላቻ ራሴን ያውጣሁ፣ የትናንቱን ታሪክ ስተርክ የተደበቀው ታሪክ ወጣቱ እንዲያውቀ ለማድረግ እንጂ ጥላቻ ለመስበክ እንዳለሆነ በግልጽ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ። ስለሆነም ስለ ኢህ አፓ ዛሬ ምስክርነቴን ስሰጥ ታሪክ በታሪክነቱ በትክክል ተጽፎ እንዲቀመጥ ከመፈለግ እንጂ ጥላቻ ለመስበክ እንዳልሆነ አውቃችሁ ትረካውን ልብ ብላችሁ እንድትከታተሉ በትህትና እጠቃለሁ። ክፍል 2፣ በደርግ መውደቂያ ከ 1980 ጀመሮ የነበረ የጸረ ደርግ ትግል ምን ይመስል ነበር ይጀላችሁ እቀባለሁና እስከዛው በቸር ሰንብቱ፣ ምልካም እሁድ ለሁላችሁ።

ክብርና ሞገስ ለሁሉም ባመኑበት ዓላማ ለወደቁ ሰማዕታት!!!"